## ገቢር ስምንት

በእጅ ላይ ቀለበት ይታያል

ናንሲ - (የድካም ድምጽ ታሰማለች)

አልዩ - ደህና! ውጤታማ የሆነ እርምጃ ነበር

ናንሲ - በእውነት ጥቂት ጥሩ ነገሮችን ገዝተናል

አልዩ - አዎን!

ናንሲ! - ጥሩ! አዲሱን ልብሴን እሞክረዋለሁ

አልዩ - እሺ! የእኔ ምላሽ - አድርገሽው ማየት ነው

አልዩ - ዋው!

ናንሲ - እንዴት ነው ጥሩ ሆኛለሁ?

አልዩ - እጅግ በጣም ጥሩ ሆነሻል::

ናንሲ - እውነት?

አልዩ - አንኚ እኮ በዓለም ላይ ካሉ ልጃገረዶች ተወዳዳሪ የለሽም.. እ!

ናንሲ - ያው ስንጋባ ከዚህ የበለጠ እንደምትሆንልኝ ተስፋ አደርጋለሁ

አልዩ - በእርግጥ አደርገዋለሁ! ሌላም የምትደነቂበት ነገር እኮ አለ

ናንሲ - ነው እንዴ?

አልዩ - ሌላ ነገር አምጥቼልሻለሁ. . .

ናንሲ - ሄይ! የደበቅኸው ነገር ምን ይሆን?

አልዩ - ኸሀ

ናንሲ - እስኪ ልየው! አሳየኝ

አልዩ - እሺ! ወደድሽው?

ናንሲ - (ትቀጥላለች) በጣም!

አልዩ - በጣም ግሩም አይደል?

ናንሲ - እሺ ግን ይሄ ሁሉ ስጦታ ለምን በአንድ ቀን ሆነ?

አልዩ - በጣም እወድሻለሁ

ናንሲ - እርግጠኛ ነህ ሌላ ምንም ዓላማ የለህም?

አልዩ - አሁን በጣም ተጠራጣሪ ሆንሽ!

ናንሲ - እም!! ልሞክረው እስኪ

አልዩ - እኔ እቆልፍልሻለ...አ. . .ዎ!

ናንሲ - እም! ቆንጆ ነው

ኧሽ አልዩ ምን እያደረግክ ነው? እየው እስኪ

አልዩ - አ! በጣም ተስማምቶሻል

ናንሲ - በጣም ጣፋጭ ነህ እኮ

አልዩ - ታውቂያለሽ! በእርግጥ እፈልግሻለሁ

ናንሲ - አይ! ከዚህ በፊት ነግሬሃለሁ

አልዩ - ሂይ! ለምን አይሆንም ግን.. እባክሽ እንቀጥል

አሁን ብቻ . . .

- አንቺም እኔ የምፈልገውን ያህል እንደምትፈልጊው አውቃለሁ ደሞም ቀለበት አስረናል

ናንሲ - እም!

- ቀድሜ እንዳልኩት እስከምንጋባ ድረስ መቆየት እንደምፈልግ አስቀድሜ ነግሬሃለሁ::

አልዩ - አ! አንዴ ልንፈጽመው እንችላለን

- ሂይ! ሣራና ጓደኛዋ ሳይጋቡ ፈጽመዋል:: ፋቱ እና ቡባም እንደዚሁ

- እኛን ተመልከች . . . እዚህ ላይ ፍፁም ችግር አይገጥመንም

ናንሲ - አዎ! የአባለዘር በሽታዎችን፣ እርግዝናን ከዚህም በላይ ኤድስን እንደሚከላከል አውቃለሁ

- ግን ይህ ችግር አይደለም! ለሁለት ዓመት ያህል በጓደኝነት ብንቆይም እስካሁን እኔን ያወቅሽኝ አልመሠለኝም

ናንሲ - (ቀጥላለች)

- አሃ የስጦታውም ምክንያት ይሄ ሳይሆን አልቀረም

- እዚህ ላይ! እርግጥ ነው ቤተሰቦቼ ደሃ ናቸው ግን በስጦታ ልትደልለኝ አትችልም! ለእኔ በእርግጠኝነት ምኑ እንደሚጠቅመኝ ታውቃለህ?

- እነግርሃለሁ እሺ! ከጋብቻ በፊት መታቀብ ከዚያም ለጓደኛ ታማኝ መሆን. . .

- ይህ የእኔ ኤድስን የመዋጋት ዘዴ እና ለፍቅሬ የምሰጠው ዋጋ ነው

- ምናልባት እነዚህ ሃሳቦች ኋላቀር ሊመስሉህ ይችላሉ ምናልባትም ሊሆን ይችላል ይሄ ግን የኔ ሐሳብ ነው

- ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብህ መወሰን ሃሳብህንም የመቀየር አዝማሚያ ያንተ ፋንታ ነው

አልዩ - ጠንካራ እመቤት ነሽ …ናንሲ!

*******